# ግንቦት 7 ቀን ይከበር!

ዑስማን ሙሉአለም ከሐራ

### መግቢያ

የካቲት 11 የህወሓት ልደት ቀን ነው። ህወሓት ብዙ ወዳጆችም ጠላቶችም ያፈራች ድርጅት ናት። 'በህወሓት ዓላማዎች ጥቅማችን ተረጋግጧል ወይም ይረጋገጣል' እንደዚሁም 'ተመሳሳይ ዓላማ አለን' ብለው በቅርብም በሩቅም አብረዋት የተሰለፉ ሁሉ ወዳጆች ሁነው ቆይተዋል። አሁንም ናቸው። 'የህወሓት ዓላማዎች ጥቅማችን የሚጎዳና የሚፃረር ነው' ብለው የተደራጁም ያልተደራጁም ሃይሎች ጠላቶች ሁነው ቆይተዋል። አሁንም ናቸው። 'ፍቅር፣ መደመር፣ አንድነት፣ ይቅርታ፣ ምህረት፣ ዕርቅ … ወዘተ' በማለት እነዚህ ሀይሎች ከጠላትነት ወደ ወዳጅነት ይቀየራሉ ብሎ ማሰብ 'አይጥና ድመት፣ ጅብና አህያ፣ አንበሳና የሜዳ ፍየል ይፋቀራሉ፣ አንድነት ይፈጥራሉ፣ ይታረቃሉ' ብሎ እንደማሰብና እንደማመን ይቆጠራል። ስለዚህ የህወሓት መወለድ በየዓመቱ ልደት መከበር የሚያስደስታቸውም የሚያስከፋቸውም መኖራቸዉ የሚያስገርም አይደለም።

ጥቅምት 23 ለጃንሆይ እና ለባላባቶች፣ መስከረም 2 ለደርግና ለኢሰፓ፣ ግንቦት 7 ለጥገኞችና ለኒዮ-ሊበራል ተላላኪዎች እንደልደት ቀናቸው እንደሚደሰቱት እነዚህን ቀናት አምርረው የሚጠሉና የሚታገሉ መኖራቸውም የሚያስገርም ሊሆን አይችልም። አሁን ባለንበት ወቅት ደግሞ እነዚህ ሀይሎች አንድ ሆነው በአንድ ድምፅ በህወሓትና በወዳጆቹ ላይ ዘምተዋል። አንድ መሆናቸውም የሚገርም አይደለም ሰፊ ልዩነት ስላልነበራቸው። አንድ ቢሆኑም ቅሉ የሚያስቸግራቸው ግን መጨረሻ ላይ ወንበርዋ ላይ ማን ይሰየም? የሚለው ነው። አሁን በንቃት የሚመራቸው የዘውድ ስርዓት ወይም የሶቭየት ሶሻሊዝም አይዶሎጂ ሳይሆን የኒዮ-ሊበራሊዝም ጥገኝነት አስተሳስብ ሆኖ በግንቦት 7 ድርጅት አስተባባሪነትና አማካሪነት አንድ ሰፊ ግንባር ፈጥረው ከሁሉም ድርጅቶች (ከኢህአዴግ ያፈነገጠውም ጨምረው) ተደማምረው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። የተሟላ ባይሆንም ትልቅ ድል አግኝተው በማእከላዊ መንግስትና በአንዳንድ ክልሎችም በትረ ስልጣኑን ጨብጠዋል። ምህረት የለሽ እርምጃም በጠላቶቻቸው እየወሰዱ ይገኛሉ። ታድያ ለዚህ ድል አንድ የበዓል ቀን አያስፈልገውም? ያስፈልገዋል። ከግንቦት 7 ቀን የተሻለ ይኖራል ብዬ ስላልገመትኩኝ ያኔ እንዲከበር ም/ቤቱ እንዲያፀድቀው ረቂቅ ማዘጋጀት ከአሁኑኑ ይታሰብበት።

### ጉዳዩ

የኢትዮጵያ ህዝቦች ዘውዳዊ አገዛዙን መጀመርያ ባልተደራጀ በኃላ በተደራጀ ግን ባልጠራ መስመርና ዓላማ ታግለዋል። የባሌ፣ የጎጃም፣ የሲዳማና የትግራይ ገበሬዎች ያመፁበት እንቅስቃሴ ነበር። በኂላም ወታደሮች፣ የዩኒቨርስቲና የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም በተለያዩ ጊዜዎች ትግል አድርገዋል። በዘውዳዊው አገዛዙ የመጨረሻ ወቅትም ያመረረ የከተማ ህዝብም በተለይም የአዲስ አበባ ህዝብ በተከታታይ ሰልፍ በማካሄድ ንጉሱ ላይ ተቃውሞውን አሰምቷል። በወቅቱ በአዲስ አበባ ሙስሊሞች የአንድ ሃይማኖት የበላይነትን የሚሰብከው ንጉስ ለመቃወም በከፍተኛ ደረጃ ተደራጅተው በብዛት ጎደናዎቹን አጥለቀለቁ። በአጠቃላይ ህዝቡ በወቅቱ ዘውዳዊ አገዛዙን እንዲወድቅ

እንዲፈረካከስ ወሳኝ ሚናውን ቢጫወትም ጠንካራና የጠራ መስመር ያለው የተደራጀ አመራር ስላልነበረው ብቸኛ የተደራጀና ሃይልና ጉልበት የነበረው የወታደሩ ክፍል ራሱን ደርግ ብሎ ሰይሞ በትረ ስልጣኑን ተቆጣጠረ።

የደርግ መንግስት ስልጣን እንደተቆጣጠረ ያለፈውን ዘውዳዊ ስርዓት እያወገዘ ለህዝቡ ብዙ የተስፋ ቃል አሰማ። 'ያለምንም ደም ኢትዮጵያ ትቅደም!' በሚል የኢትዮጵያ ህዝብ የአገር ወዳድነት ፍቅርን በመጠቀም ተቀባይነት ለማግኘት ተወራጨ። ያለምንም ደም ያለውን ቃልና መዝሙር ብዙ ሳይቆይ በመርሳት 'የፍየል ወጠጤ' ዘፈን እያሰማ የተቃወመውን ብቻ ሳይሆን አስቦ ይሆናል ብሎ የጠረጠረውን ሁሉ ያለ ፍርድቤት ትእዛዝ ማሰር ሳይሆን መግደል የሚያስችል ስልጣን ከላይ እስከ ታች ያለው መዋቅር ተስጥቶት በነፃ እርምጃ በተለይ ወጣቱ በየሰፈሩ ተረሸነ። የአንድ ትውልድ ደም በከንቱ የትም አፈሰሰ።

ይህን አሰካፊና የመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳለፈው አስከፊ ሰቆቃ ጀነራል ካሣየ ጨመዳ በ ሁቲቪ በኢህአዴግ ስም ስልጣን የተቆጣጠረው ቡድን የኢህአዴግ መንግስትን የመወንጀል በደረሰው ልብወለድና በፈበረከው ዶክመንተሪ አሰቃቂነቱን አምርረው እየውቀሱ፣ በደርግ ጊዜ የተከሰተው ግፍ ይህ ዓይነት የሚጋነን አልነበረም አሉ። ጨዋታው ሁለት ነገሮችን ግምት ውስጥ ያስገባ ነው። አንድ ህዝቡ የአጭር ጊዜ ትውስታ (short memory) ነው ያለው በማለት የነበረውና የተደረገውን እንዳልነበረና እንዳልተደረገ አስመስለህ ብታወራ ሃይ የሚል የለም ነው። ጥቂት መፅሐፍት ስለደርግ የተፃፉም ቢኖሩም የማንበብ ባህል በሌለበት አገር ብታወራ ሰሚ አታጣም ነው ነገሩ። ሁለተኛ አሁን ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ በአብዛኛው ወጣት በመሆኑ ደርግን የሚያውቅበት እድል አልነበረውም። ደርግ በህዝብ ትግል ከስልጣን ከተገረሰሰ 27 ዓመት በላይ ባስቆጠረበት ስሌት ያኔ እድሜው 10 ዓመቱ የነበረ ህፃን ዛሬ 37 እና ወደ አርባው ዓመት እየተጠጋ በመሆኑ ካልተነገረውና መፅሓፍ ካላነበበ ስለ ደርግና ኢህአዴግ ልዩነት ሊያቅ አይችልምም የሚል ታሳቢ ያደረገ ነው። በተጨማሪም ኢህአዴግ ስለ ደርግ ሲናገር ለምን ከመጥፎና ከወደቀ ጋር ራሱን ያወዳድራል? የሚል የራሳቸው የደርግ ካድሬ ፕሮፖጋንዳ ወጣቱ ሰለባ የሆነበት ሁኔታ ሲፈጠር የመንግስት ሚድያዎች ወጣቱ የትላንት የአገሩ ስርዓት ምን መስል እንደነበረና ከየት ተነስቶ አሁን ያለበትን ሁኔታ እንደደረሰ እንዳያውቅ በቅጡ ሳይሰሩበት ስለቀሩ ነው። ይህ ክፍተትን ደግሞ የደርግ ርዝራዦች እነ ካሳየ ጨመዳ ሊጠቀሙበት እየተውተረተሩ ይገኛሉ።

ይሁን እና ህገ መንግስቱ ሁሉም የዲሞክራሲ መብቶች ሲያረጋግጥ ነፃ ፕሬስ ሲታወጅ ቀድመው በመሳርያ ሃይል ህዝቡን ማንበርከክ ያልቻሉት የደርግ ካድሬዎች ነበሩ ቀድመው ለህዝብ የነፈጉትን የመፃፍ ነፃነት ተጠቃሚ ሁነው በነፃ ፕሬስ መብት ጋዜጣ የጀመሩት። የተቃውሞ፣ የውሸት፣ የፈጠራ እና በደርግ መውደቅያው ዋዜማ በጎንደር አደባባይ 'ትግሬ ገዳይ' ያለውን ዘረኛ መፈክር አንግበው እስካሁን በአንድ ህዝብና ድርጅት እንዳሸቸው እየፃፉና እየዘመቱ የሚገኙት። ተከታታይ የነበረውን የልማትና የዲሞክራሲ ለውጦች እንደሌሉ የሰበኩት መቶ አለቆች እንደነ ሲሳይ አጌና የመሳሰሉ ናቸው። እነሱ በህዝብ ትግል የተገኘውን ዲሞክራሲ እያጣጣሙ ዲሞክራሲ የለም ብለው ይጮሀሉ። የኢህአዴግ መንግስት ስለ ደርግ እንዳይናገር ወይም በተከታታይ እንዳያጋልጥ ጫና ፈጥረው መድረኩን በብቸኝነት ተቆጣጥረው ለሀያ ሰባት ዓመት ፀረ ኢህአዴግ በተለይም ሚልዮን የሚጠጋ ቁጥር የነበረውን የደርግ ሰራዊት ማንበርከክ ላይ

የአንበሳውን ድርሻ የነበረውን ህወሓትን እያጠቀሩ ያሉት:: የደርግ ሰራዊት ሳይሆን የኢትዮጵያ ሰራዊት ነው:: የኢትዮጵያ ዳርደንበር ጠባቂ ነው ብለው ሰበኩ:: መንግስቱ ልዩ የአገር ፍቅር የነበራቸው መሪ አድርገው ክበው የሌለ ገፅታ ሰጡት:: በጦር ግንባር የተሸነፈ፣ የተማረከና ሸሽቶ የፈረጠጠ ድሮስ ምን እንዲያወራ ይጠበቃል! ገበናውን ከመደበቅና ጠላቱን ደግሞ ጥላሸት ከመቀባት ውጭ ምን ይላል:: በዚህ መንገድ ህዝቡን በተለይም ወጣቱን መረዙት:: ቀላል የማይባል የኢህአደግ አባልም የዚህ ሰለባ ነው:: ጥፋቱ ግን የራሱ የኢህአዴግ መንግስት ነው:: ልሳኑ ዘግቶ ስራዬና ተግባሬን አይቶ ህዝቡ ይከተለኛል የሚል ፈሊጥ ይዞ የኖረው:: ስለዚህ ደርግን የመሰለ ፋሽሽት አንድን ትውልድ የገደለና ያጎደለ ማሞካሸት ምን ያህል ፀረ ህዝብነትና ወንጀል እንደሆነ አሁንም ቢሆን መሰራት ያለበት ጉዳይ ነው:: አሁን የተተወና የተገላቢጦሽ ደርጎቹ እንደተለመደው ዘራፍ የጀመሩ ቢመስልም::

ደርግ በከተማ በኢሠፓ ሲታወቅ በገጠር ገበሬው እሰገድ በሚል ይታወቃል:: የገበሬውን ምርት ገና በአውድማው እያለ 'ላንተ ይህ ይበቃሃል'፣ 'የቀረውን ለእሰገድ አስረክብ' በሚል በጣም ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ ራሳቸው እየተመኑለት ይወሱድበታል:: ይህ እያደረጉ ሲያስቸግሩት ገበሬውም ትንሽም ብዙም ባመርት ተጠቃሚ ካልሆንኩኝ ምን አለፋኝ በማለት መለገም ጀመረ:: ተቃውሞም መሆኑ ነበር:: ዋነኛ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በእርሻ ስለነበር የደርግ የእዝ ኢኮኖሚ ተንኮታኮተ:: ህዝቡም ለችግር እና ለራሽን ወረፋ ተዳረገ:: ደርግ ከከተማውም ከገጠሩ ህዝብም ተጠልቶና ተነጥሎ ስለነበረ በኢህአዴግ መሪነት ህዝቡ ከጫፍ እስከ ጫፍ ታግሎ ደርግን ገረሰሰው:: የደርግ ቁንጮ መሪ ኮ/ል መንግስቱ ሃይለማርያም እንደ ኢድአሚን፣ ሂትለር፣ ሞሶሎኒ ጨካኝና ፋሽሽት ነበሩ:: እንደነ ጀ/ል ታሪኩ የደርግ ቀኝ እጅ የነበሩትን ለማጥፋት የተጉት የሚበልጣቸውና የማይፈሩዋቸውን ገለል ማድረግ ፋሽሽቶች ስለሚወዱ ረሽኑዋቸው:: አሁን በማወቅም ባለማወቅም የዚህን ፋሽሽት ፎቶግራፍ በመኪናቸው የሚለጥፉት ታሪኩን ለመሸፋፈን ነው:: አሁን ምድረ አጎብዳጅ የነበረ ታሪክ ተናጋሪ የሚሆንበት ምክንያት ብዙ ስላልተፃፈና ጥቂት የተፃፉትም እንዲነበቡ ስራ ስላልተሰራ ነው::

ደርግ ከተገረሰሰ በኃላ የተደረገውም ጭምር የማያቅ ትውልድ ነው ያለው:: ስላልተፃፈ እና የተፃፈም ካለ ስለማይነበብ ነው:: በስመ ነፃ ሚድያ የለየላቸው ተቃዋሚ ሳይሆኑ ጠላቶች የተቆጣጠሩት ስለነበር:: ከደርግ በኃላ ያለውን ለውጥ መዘገብን ይቅርና የታየው አወንታዊ ለውጥ ሲመለከቱ አይናቸው ደም የሚሞላ ናቸው:: የተቆጣጠሩት ብዕርና ልሣን ውሸትና አሉታዊ ገፅታ ብቻ ላይ የተመሰረተ ስለነበር ትውልዱ ከደርግ በኃላም ያለውን ታሪኩም በአግባቡ እንዳያቅ ተደርጓል:: እንኳን ወጣቱ ግምቶ ሙሁራንም የዚህ ሰለባ ሁነው ቆይተዋል:: ለምሳሌ ግልፅነታቸውን እያደነቅኩኝ መራራ በቅርቡ የአቶ በረከትን መፅሐፍ 'ጨርሰው እንዳላነበቡት' ወይደሞ የተወሰነ ክፍሉን ብቻ እንዳዩት ተናገሩ:: ለምን የተወሰነ ክፍሉን ብቻ ያነባሉ? ይህ ነው የብዙ ሰው ባህል:: ሳታቀው መተቸት ይቀናናል:: ጨርሰን ሳናነብና ሳንረዳ ተረት ተረትን ታሪክ ብለን እናወራለን::

ከደርግ በኃላ ምን ተፈጠረ? ኢህአዴግ ስልጣን በብቸኝነት የያዘው ለአንድ ወር ነው:: ደርግን ተዋግቼ የደመሰስኩት እኔ ነኝ ብሎ እንደ ጎረቤቶቻችን ሻዕብያ እስካሁን ራሱን ያለ ህዝብ ፍቃድ ስልጣንን በብቸኝነት አልያዘም:: ኢህአዴግ የደርግ መደምሰስ የሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ድል እንደሆነ ነው የሚያምነው:: ለአንድ ወር በግዚያዊ መንግስት ያስተዳደረውም ወደ ሚልዮን የሚጠጋ ከነመሣርያው የተበተነ ሰራዊት የነበረበት አገር

ሰላምና መረጋጋት ስለማይኖረው የሰላምና የማረጋጋት ስራ ለመስራት ነበር እንጂ እንደ ደርግ እድሜውን በግዚያዊ መንግስት ለመጨረስ አልነበረም። አብዛኛው የደርግ ሠራዊት ተገዶና ያለውዴታው የተመለመለና ከስራውም ከቤተሰቡም የተፈናቀለ ስለነበረ ይህንን ማረጋጋትና የወደፊት ተስፋው ምን እንደሆነ ማሳየት ይገባ ስለነበረ እንዲመዘገብና ትጥቅ እንዲያስረክብ ብሎም ወደ ሲቭልነት ተመልሶ እንዴት እንደሚቀላቀል እና በምን መንገድ መልሶ እንደሚቋቋም ለዚህ ስራ ተብሎ በተቋቋመ ኮምሽን አማካኝነት ስራውን በመስራት መጀመርያ ሰላም ለማረጋገጥ ነበረ። ይህም ያስፈለገበት ምክንያት በየአካባቢው ዝርፍያና ስርቆት ተበራክቶ ስለነበር ህዝቡን በማሳተፍና በማስተባበር በየአካባቢው ህዝቡ የወከላቸው የሰላምና መረጋጋት ኮሚቴ ተደራጅተው በወቅቱ ከነበረው የኢህአዴግ ታጋይ ሠራዊት በመተባበር ሰላምን ማረጋገጥ የተቻለበትና የተዘረፈ ትጥቅም ንብረትም በአጭር ጊዜ የተመለሰበት ሁኔታ ነበር።

ከአንድ ወር በኃላ የኢህአዴግ ግዚያዊ መንግስት ተሽሮ በቻርተር የሚመራ በኢትዮጵያ በወቅቱ ተድራጅተው የቆዩና በወቅቱም ተራሩጠው ራሳቸውን ያደራጁ አገርቤትም የነበሩ ውጭም የቆዩ የተሳተፉበት የሽግግር መንግስት ተመሰረተ። ተልእኮውም ህገመንግስት ተረቆ የህዝቡ ተወካዮች ህገ መንግስታዊ ጉባኤ አድርገው ካፀደቁ በኃላ በህገ መንግስት መሰረት ምርጫ ተካሂዶ አሸናፊው ፓርቲ በህዝቡ ይሁንታ ስልጣን እስኪይዝ ድረስ አገሪቱን ማስተዳደር ነው። የሚመራውም ሁሉም ፓርቲዎች በጋራ ባፀደቁት ቻርተር መሰረት ነበር። በዚህ መንገድ ህዝባዊ ምርጫ እስኪካሄድ የሽግግሩ መንግስት አገሪቱን የመራት። በቀጣይም ህገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽንም ተቃቁሞ ስራውን ጀምሮ ረቂቅ አዘጋጀ። የህገ መንግስቱ ረቂቅ እንዳለ በሊህቁ ተዘጋጅቷል ተብሎ ይፅደቅ አልተባለም። በመላው አገሪቱ ለመጀመርያ ጊዜ በህዝቡ ንቁ ተሳትፎ፣ ውይይትና ክርክር ከተደረገበት በኃላ ከመላው ህዝብ በተወከሉ በህገ መንግስታዊ ጉባኤ ፀደቀ። ‘ያልተማረና የህግ እውቀት የሌለው ህዝብ ተወያይቶ የፀደቀ ህገ መንግስት ነው’ ለሚሉ ሃይሎች መልሱ የህዝቡን ውይይት የሚያሳዩ ዶኮመንቶችና ኢዲት ያልተደረጉ ፊልሞችን በማየትና ቃለ ጉባኤዎቹን በማንበብ ህዝቡ ለጥቅሙ ምን ያህል ብስለት እንደነበረው መረዳት ይቻላል። ህዝቡ ጥቅሙን መቼም ቢሆን እንደማይስት ማረጋገጫ ነውና።

ከህገ መንግስቱ መፅደቅ በኃላ ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ተካሄደ። ኢህአዴግ አብላጫ ድምፅ አግኝቶ ስልጣን ከያዘ በኃላ ዲሞክራሲ በተግባር የተረጋገጠበት ሁኔታ ታይቷል። የመደራጀት፣ የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመቃወምና የመሰለህን እምነትና አመለካከት የመያዝና የማራመድ መብቶች ተረጋገጡ። ከህዝቡ በተጨማሪም በዋናነት የፋሽሽቱ ደርግ ርዝራዦች የተጠቀሙበት ሁኔታ ነበር። ዜጎች በመሆናቸው ህገመንግስታዊ መብታቸው ተከብሮላቸዋል። በልማቱም የደርግን የእዝ ኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና መመርያዎችን ብቻ በማንሳት ኢኮኖሚው ህይወት ዘራ። የመጀመርያዎቹ አመታት አነስተኛም ቢሆን አገሪቱ ለመጀመርያ ጊዜ በተከታታይ አውንታዊ ዕድገት አስመዘገበች። በዚህ ሁኔታ እያለ አገሩን ማስተዳደር ያቃተው የኤርትራ መንግስት/ ሻዕብያ በእብሪት ጦርነት ከፈተብን። በህግ ጉዳዩ ይዘን ጦርነቱን ለማስቀረት በርዋንዳና በአሜሪካ መንግስታት የተደረገው የሽምግልና ጥረት የሻዕብያ መንግስት ፍቃደኛ ባለመሆኑ ተገደን ወደ ያልተዘጋጀንበትና ያልፈለግነው ጦርነት ገባን። መዳን ጀምሮ የነበረው ኢኮኖሚ እንደገና የልማት ሃይል የሆነውን የሰው ሃይልና ያፈራውን ሃብት የሚያወድም ጦርነት በመግባታችን ችግር ላይ መውደቁ አልቀረም። በእብሪት ወረራ የፈፀመብንን ሃይል

ለመመከት በተደረገው የመከላከል ጦርነት የኢትዮጵያ ህዝቦች ሁሉም በአንድነት ቆመው የተሰለፉበት ስለነበር በሃይል ተይዘው የነበሩ አካባቢዎች በአሸናፊነት ለማስመለስ ተችላል።

ይህ ድል ብንጎናፀፍም ውስጥ ለውስጥ እያደጉ የቆዩ ዝንባሌዎች ጎልተውና ገንፍለው በመውጣት በጦርነቱ ዙርያና በጠቅላላው የአገሪቱ የወደፊት አቅጣጫ (አጀንዳ) ላይ በራሱ በኢህአዴግ በተለይም ህወሓት ውስጥ ልዩነት ተፈጠረ። ልዩነቱ የጦርነቱ ዓላማና አገራችን ውስጥ ከጦርነቱ በፊት የነበረን ጉዞና ቀጣይ አቅጣጫ ላይ ነበረ። ይህን ልዩነት ለመፍታት የተለያዩ ዕህፎች ተዘጋጅተው ረዘም ያለ ክርክርና ውይይት ተካሂዶ በድርጅቱ አሰራር መሰረት በአብላጫ ድምፅ የበለጠ ድምፅ ያገኘው ወገን ቀጣይ ሰነዶች ላይ ለመወያየት ስብሰባው አደራሽ ሲገኝ ራሱን ከድርጅቱ አሰራር ውጭ ውስጥ ለውስጥ ድርጅት ውስጥ ሌላ ድርጅት አደራጅቶ የቆየው ሃይል በስብሰባው ሳይገኝ ቀረ። በሰለጠነ መንገድ ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት ተጀምሮ የነበረውን ጥረት አኮላሸው። ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ቀውስ ተፈጠረ። ቀውሱን ለመፍታትና ውይይቱን ለመቀጠል ስለተቸገረ ስብሰባው እንዴት እንደተቋረጠና መፍትሔ ፍለጋ ወደ ካድሬው ወርዶ ውይይት ሲደረግ በቀጥታ ጉባኤ ይደረግ ብሎ ድርጅቱ ባልተዘጋጀ አጀንዳ ጉባኤ ተድርጎ ለመከፋፈል ስለከጀለ ቤቱ ስላተቀበለው በድምፅ የተሸነፈው ቡድን በድርጅት ውስጥ ሌላ ድርጅት ፈጥሮ በድብቅ የተደራጀው ቡዱን በድጋሚ መድረክ ረግጦ በመውጣቱ ለውይይትና ለክርክር ምንኛ እንዳልተዘጋጀ በካድሬው ፊት ተጋለጠ። በቀጣይነት በህወሓትም በሌሎች እህት ድርጅቶችም ሰፋፊ ውይይቶች ተካሂደው ስለ ጦርነቱ ግምገማ ተካሂዶና ስለ ቀጣይ የአገራችን ቀጣይ የለውጥ ጉዞ አቅጣጫ ተቀይሶ ሰፊ የተሃድሶ እንቅስቃሴ በመላው ድርጅት አባላትና በህዝብ ተካሄደ። በዚህ የተሃድሶ መስመር መሰረት በተደረገ እንቅስቃሴ በአገራችን ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ተከታታይና ሁለት አሃዝ ያለው ሁለገብ ለውጥ ተመዘገበ።

ነገርግን ይህ ሂደት ገና ወደ ተግባር ሳይገባና የተሃድሶ ሐሳቦቹ የማስረፅ ምዕራፍ ላይ እያለ በነበረው የ1997 አገራዊ ምርጫ ላይ ኢህአዴግ በህዝብ ተመርጦ ስልጣን በያዘባቸው ዓመታት ህዝቡ የጠበቀውን ለውጥ ባለማስመዝገቡ በተለይም በከተሞች የሚጠበቀው ያህል የህዝብ ድምፅ ያጣበት ነበር። በአጠቃላይ ግን በማስጠንቀቅያ አገሪቱን ሊያስተዳድር አብላጫ ድምፅ ያገኘበት ሁኔታ ነበር። ይህ ሁኔታ ኢህአዴግን የበለጠ ተሃድሶውን ፈጥኖ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ያመላከተና የተሃድሶው አስፈላጊነትና ወቅታዊነት ያረጋገጠ ነበር። በአገራዊው ምርጫ ተሳትፈው የነበሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ከማሕበራዊ መሰረታቸውና በኢህአዴግ የለውጥ ፍጥነት ያልተደሰተው የራሱ የኢህአዴግ ማሕበራዊ መሰረትም ሳይቀር በከተሞች ቀላል ቁጥር የማይባል ድምፁን ችረውቸው ነበር። ተቃዋሚ ፓርቲውቹ አዲስ አበባ ላይ አብላጫ ድምፅ አግኝተው ማስተዳደር የሚችሉበት እና በተወካዮች ም/ቤትም ቀላል ያልሆነ መቀመጫ ያገኙበት ሁኔታ ነበር። በክልሎችም በተለይም በአማራ ክልልም አብላጫ ድምፅ ባያገኙም ከፍ ያለ ድምፅ አግኝተው ነበር። ይህ ክስተት ህገ መንግስቱ የዲሞክራሲና የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት እውን ያደረገ መሆኑ ያረጋገጠ ነበር። ተቃዋሚዎቹ ይህን ያገኙትን ድምፅ ተጠቅመው የህዝቡን ቀጣይ አመኔታ ለማግኘት ጥረት ማድረግ ሲገባቸው ከተቃዋሚዎቹ ውስጥ ብዙ ድምፅ አግኝቻለሁ የሚል ወገን በተለይም ቅንጅት ብሎ ራሱን አደራጅቶ የነበረው ስብስብ ምርጫው ተጨብርብራል በሚል በምርጫ ያጣውን ድምፅ መቀበል ተስኖት የፈረንጅ ምስክርነት እንደ ማረጋጫ

ይዞ ከምርጫ ውጭና በነውጥና ይህን ያህል አስገድለን ስልጣን ላይ እንወጣለን የሚል ሂሳባዊ ስሌት ሰርተው በተረጋጋና በሰከነ ፖለቲካ ጉዞ የነበረችውን አገራችን ወደ ብጥብጥና አሳፋሪና ዘግናኝ የርስበርስ ፍጅትን ሊያስከትል የሚችል ዘርን መሰረት ያደረገ ቅስቀሳና የነውጥ እነቅስቃሴ ገቡ።

ከነበረው የከረፋ የዘር ቅስቀሳ በህዝቡ አስተዋይነት፣ የኢህአዴግ መንግስት ከስሜት በፀዳ መንፈስ በሰጠው አመራርና መቻም መዘንጋት የሌለበት ከተቃዋሚው ጎራም 'ያገኘነውን ድምፅ ተጠቅመን እየተቃወምን ህዝቡ የሰጠንን ድምፅ አክብረን ም/ቤቱ ውስጥ መሳተፍ አለብን በአዲስ አበባም መንግስት መመስረት አለብን' ብለውና የነውጡ መንገድ አንከተልም ብለው ፅኑ አቋም በመያዛቸው ብዙ ስም ቢሰጣቸውም አገሪቱ ሰላምና መረጋጋት አግኝታ ወደ ተጀመረው ከፍታ ወዳለው የለውጥ ጎደና እንድትገባ አስተዋፅኦ በማድረጋቸውም ተፈርቶ የነበረው አደጋ ለመሻገር ተችሏል። የነውጡን መሪዎች ተጠያቂ ማድረግና ፍርዳቸውን ፈፅመው ተቅጥተው እንዲወጡ ማድረግ ይቻል የነበረ ቢሆንም ለጀማሪ ዲሞክራይታይዘሽን ያልሆነ ትምህርት እንዳያስተላልፍ በሚል ሆደሰፊነት ምህረት ጠይቀው እንዲፈቱ ተደረገ። ምህረት የማድረጉ መንገድ ለደርግ ባለስልጣናትም ተርፎ ለህዝቡ የነፈጉትን በፍ/ቤት መዳኘት መብት በህገ መንግስቱ ተረጋግጦላቸው ተከራክረው በማስረጃ ተረተው ተፈርዶባቸው የነበረ ቢሆንም የሞት ፍርድም ተቃልሎ በምህረት ነፃ የወጡበት ዕድል አግኝተዋል። ወጥተውም አዲሱ ስርዓት ያረጋገጠውን ዲሞክራሲያዊ መብት ተጠቃሚ ሁነው ፋሽሽታዊ የደርግ ስርዓትን እና የፈፀመውን ግፍ የሚሸፋፍንና እንዲያውም የሚያመካሽ መፅሓፎች ለመድረስም ችለዋል። ከደርግ መገርሰስ በኃላ የመጣውን ተጨባጭ ለውጥ እያዩ ግግም ብለው የእኛ ስርዓት ይሻል ነበር በማለታቸው የአዲስ አበባ ቀልደኞች ባለስልጣኖቹ ሲፈቱ ምን እንዳሉ የቀለዱት ገላጭ ነው። "ኢህአዴግ የያዘንና ያሰረን አዲስ አበባ ሆኖ የፈታን ግን ሌላ ከተማ ላይ ነው" አሉ ብለው መሳቂያ አድርገዋቸው ነበር።

ኢህአዴግ ከውስጥም ከውጭም ብዙ እንቅፋት ቢገጥመውም አሰስ ገሰሱን ለመፍታት ብሎ ስራ ሳይፈታ በዋናነት ድህነትን መዋጋት ላይ ነበር የተረባረበው። ድህነት የሁሉም ችግሮች ምንጭ ነው ብሎ ያመነው ኢህአዴግ ለአንድ አፍታም ቢሆን አይኑን ሳይነቅል ህዝቡን አስተባብሮና ደግፎ ስለተረባረበ ለአስራ ሁለት ዓመታት ያህል ተከታታይና ፈጣን ዕድገት በማረጋገጥ የተሃድሶ መስመሩ ምንጭ የሆነው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ፕሮግራም ትክክለኛነት አስመስክሯል። የህዝቡና የአመራር ቁርጠኝነትም ይህንን ፍቱን መድሓኒት ተግባራዊ እንዲሆን ወሳኝ ሚናቸውን ተጫውተዋል።

አገሪቱ በዚህ የለውጥ ጎደና እያለች በውጭ ሃይሎች የሚደገፉ የፀረ ሰላም ሐይሎች የማደናቀፍ ስራም እንደቀጠለ ነበር። በተለይም በኤርትራ ሰፍረው ፀረህዝብ ተግባራቸውን በትጥቅና በሽብርተኝነት ማካሄዳቸው አልተውም ነበር። በሁሉም የሚድያ ውጤቶች በሚባል ደረጃ ተጨባጭ ዕድገት እያረጋገጠ ያለውን አብዮታዊ ዲሞክራሲ ላይ አንዴ የኮሚኒስት አስተሳሰብ ነው፣ አንዴ የዘረኛ ህወሓት ፍልስፍናና ፀረ አንድነት ነው፣ አንዴ በኢኮኖሚ እንጂ በዲሞክራሲ ለውጥ አልተመዘገበም፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የለማችው ትግራይ እንጂ ሌሎች ክልሎች ሃብታቸው እየተዘረፉ ነው እና ብዙ በየጊዜው የሚቀያየሩ በሬ ወለደ ውሸቶችን ተጠቅመው ባለ መታከት ህወሓትና የትግራይ ህዝብ ለማጥቆር ቀንና ለሊት ለዓመታት ሲሰሩ ቆይተዋል። ህወሓትን ጥላሸት ለመቀባት የሚደረድሩት ማስረጃ የራሳቸውን ማንነት ብቻ በትክክል የሚገልፅ ነው እንጂ

ህወሓትን የመሰለ የህዝብ ድርጅት አይገልፀውም ብቻ ሳይሆን ጭራሹንም አይመለከተውም። ይሁንእንጂ ለዚህ አሉታዊ ገፅታ መስፋፋት ህወሓትም የራሱ ድርሻ ነበረው ማለት እንችላለን። ጠንክሮ ባለመመከቱና ትክክለኛ ግንዛብ እንዲፈጠረ ባለመስራቱ።

ስልጣን ላይ የነበሩትም ሆኑ አዳዲስ የስልጣን ናፋቂውችም ለምን ህወሓትና አብዮታዊ ዲሚክራሲ ላይ ይረባረባሉ? ያለ ምክንያት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱ ጥቅማቸው የሚፃረርና ትላንትና በከፍተኛ መስውእትነት ህዝቡን አስተባብሮና አታግሎ ያሸነፋቸውን ሃይል ቢጠሉ ምክንያታዊነት የላቸውም አይባልም። በጥቅማቸው የመጣባቸውን ካልጠሉ ማንን ይጥሉ? የጎደለ ጥቅማቸውን ለማስመለስ ውድቀቱን ቢመኙና ለውድቀቱ ቀንና ሌሊት ቢለፉ፣ ቢታገሉና ቢተጉ በነሱ አይን ካየነው ባሕሪያዊና ተፈጥሮአዊ ነው። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሐይል ደከምከም ሲል ብቻ ሳይሆን ችግር ላይ ይሆናል ብለው ሲያስቡ የተቀሙትን ጥቅም ለማስመለስ ጥረት ማድረጋቸው የግድ ነው። ስለዚህ ሁሌ አይናቸውና አፋቸው ከፍተው ይሳካላቸው አይሳካላቸው ይሞክራሉ። ይጠባበቃሉ።

አህአዴግም እነዚህን የጥላሸት ቅቦች መከታተል ላይ አልነበረም ዋና አቅጣጫውና ተግባሩ አድርጎ የተንቀሳቀሰው። ለነዚህ የተመቻቸ ሜዳ እንዳይፈጠር ማድረግ ላይ መረባረብ ነበር ቁልፍ ስራው ያደረገው። የተመቻቸ ሜዳ የሚባለው መጀመርያ ኢህአዴግ ውስጡ ጥራትና ህዝባዊነት ይኖረው ዘንድ ባለማቋረጥ ለደቂቃም ሳያርፍ የውስጥ ትግል ማካሄድ እንዳለበትና በተለይም ከፍተኛው አመራር ውስጥ ማተኮር እንዳለበት የተሃድሶ መስመሩ በአፅንዖት ያሰፈረው። ከዚህ ተነጥሎ የማይታየውና መሰረታዊ መፍትሔም የሆነው የተሃድሶውን ጉዞ በላቀ ፍጥነት በመምራትና ለውጥ በማስመዝገብ ሽግግር እንዲረጋገጥ በማድረግ ወደ ኃላ የማይመለስበት ሁኔታ ለመፍጠር ቀንና ሌሊት ሲተጋ የነበረው። ተከታታይ ዕድገት የተመዘገበውም እነዚህ ሁለት ነገሮች አጥብቆ ይዞ በመሄዱ ነው። ይሁንእንጂ እነዚህ አላማዎች ሳይሳኩ ሲቀሩ ወይ ሲዛነፉ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እና ፈጣሪው ብለው የሚገምቱትን ህወሓትን ለአንዴና ለመጨረሻ ለማጥፋት ሁሌም በእውናቸወና በህልማቸው የሚያልሙትና የሚመኙት።

በኢህአዴግ በኩል ደግሞ በሂደት ነገሮች በመሳካታቸው ዘና ማለት ተጀመረ። ሁሉም ነገሮች እየጎደሉ ናቸው ፈጥነን እርምት እናድርግ የሚል እንቅስቃሴ በሁሉም የኢህአዴግ ድርጅቶች ይነሳ የነበረ ቢሆንም ለስልጣን ማራዘሚያ እና መወጣጫ የሚፈልግ ሐይል የተገኘው ድል አስክሮት በዚህ ድል የደነዘዘው አብዛኛው ሀይል በመጠቀም እንቅስቃሴው አኮላሸው። በተጨማሪም ትግል የጀመረውም ሐይል አደጋው ቢታየውም የአደጋው ጥልቀትና ፍጥነት በውል ያልተገነዘበ ነበር። ይህ የተዳከመ አመራር የሚመራው ለውጥ ወደፊት እያየ ሳይሆን አፍንጫው ስር ያለውን ችግር ብቻ ለመፍታት ሲያጣጥርና ነካ ነካ አድርጎ ያልፈታውን ችግር እንደፈታ ሪፖርት የሚያደርግና ባለመፈታቱ ምክንያት ሌላ ችግር ሲፈጠር ተጠያቂነት ለመሸሽ ወደ ሌሎች የሚቀስር ሆነ። በተለይ የኂላ የኂላ ራሱ የሚያስተዳድረው ክልል ውስጥ የታዩት ሁሉም ችግሮችና ድክመቶች የህወሓት አድርጎ የመቀሰር ልምድ በኢህአዴግ እህት ድርጅቶች በይፋ እየተለመደ መጣ።

ኢህአዴግ ገጥሞት የነበረ ጥልቅ ብልሽት በጥልቀት ተሃድሶ ለመፍታት ጥረት አድርጓል። ይሁን እንጂ አንዳንድ አባል ድርጅት ራሱን ለማረም ሲዳክር አንዳንዶቹ

ደግሞ በሌላ ሴራ ተጠምዶ ውስጥ ለውስጥ በድርጅት ውስጥ ሌላ ድርጅት ፈጥሮው ለስልጣን ብለው ሁሉም የኢህአዴግ መርሆዎችን ለገበያ አቅርቦው ከአገር ውስጥና ከውጭ ካሉ የኢህአዴግን ሞት ከሚመኙና አክራሪ የኒዮሊበራል ሐይሎች ተባብረው የፋይናንስና ሌሎች ድጋፎች ተደርጎላቸው ሲዘጋጁ ቆዩ። የኢህአዴግን አመራር በግለሰብ ደረጃ ፈርጀው ከማን ተቃውሞ ሊገጥማቸው እንደሚችልና እንዴት ዓላማቸውን እንደሚያሳኩ እንደ ቡድን አቅደው ተንቀሳቀሱ። ይባስ ብለወ በመጨረሻ ከኢሳያስ ጋር በምስጥር በአምባሳደር ያማማቶ አማካይነት ተገናኝተው እንዴት ስልጣን እንደሚይዙና ከያዙ በኃላ ለሚመጣ ተቃውሞ ማክሸፍና ማዳከም ብለውም ስልጣናቸውን ለማደላደል እንዲችሉ ኢህአዴግን ራሱን ማዳከምና የኢህአዴግ ስም ይዞ በሪፎርም ስም ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሃዲድ አውጥቶ ወደ ኒዮ ለበራሊዝም ጥገኛነት ከፉ! ለማደረግ አቅደው ተጉ። በዚህም እቅድ መሰረት በኢህአዴግ ም/ቤት ምርጫ አጭበርብረው ውጭ በተደረገ የተደራጀና ያለቅለት የምርጫ ውጤት ይዘው ሁሉም አውቆ ተዋናይ ያልሆነበት ምርጫ ተካሂዶ አብዮታዊ ዲሞክራሲ በዝረራ ሲሸነፍ የሁሉም ፀረ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ሃይሎች ግምባር ከ27 ዓመት የመልሶ ማጥቃት ትግል በኂላ ውጤት አስመዝግበው ስልጣን ተቆጣጠሩ። ተጭበርብሯል እንዳይባሉ በዛው ምሽት 'ድላቸውን' ተሰብሳቢው ገና ከአደራሹ ሳይወጣ ተቻኩለው አበሰሩ!

ሙሉ በሙሉ ባይሆንም አጠቃላይ ያስቀመጡት ግብ በከፊል ተሳካላቸው። ስልጣን የተቆጣጠረው ሃይል ራሱን ለማስታዋወቅ ጊዜ ሳይውስድ አጠንክሮ ተንቀሳቀሰ። ሞቅ የሚል ጭብጨባ ሲበረክትም ኢህአዴግን አየወቀሰ በኢህአዴግ ውስጥ ራሱ አደራጅቶ ታግሎ ይህን ውጤት እንዳስመዘገበ አወጀ። ደመኛ የኢትዮጵያ ጠላቶችን ኢህአዴግን በወቀሰበት አንደበት አሞገሳቸው። ስለዚህ ነው እስካሁን ብዙ ሰዎች እነሱን ኢህአዴግ አድርጎ ለማየት የሚቸገረው። የኢህአዴግ ስብሰባና ጉባኤ ሲሳተፉ ሌላ የህዝብ መድከርክ ሲደሰኩሩ ደግሞ ሌለ የሚያወሩ ሲሆንበት ህዝቡ ግራ የሚጋባው። በተጨማሪም በአክራሪ ብሄርተኝነት ስሜት ራሱ ልዩ የኢትዮጵያ አዳኝ አድርጎ ራሱን ሽሞና በህዝበኝነትም ተመርዞ ሊፈፀሙ የማይችሉ ነገሮችን እንፈፅማለን ብሎ ቃል በመግባትና የነበሩ ስህተቶች ሁሉም ህወሓትና ለምስኪን የትግራይ ህዝብ ተጠያቂ እያደረገ በመንቀሳቀስ አወናብዶ ለጊዜው የሚያሰነብተው ተቀባይነትና ዝና አገኘ። ነብዩ መጣ! እስኪባል ጭፍን ድጋፍ አገኘ። ምንም ሳይሰሩ ይህ ሁሉ ድጋፍ! ሲከዳ ደግሞ ቅፅበታዊ መሆኑ ሲጤን ያስደነግጣል። ህዝቡን ወረተኛ ብሎ እስከመሳደብ ያደርሳል። የለውጥ መሪ ነን ባዮች መርህ የተገኘችው መድረክ ተጨብጭቦልህ እንደምንም ማለፍ ነው። ህዝብ የማስታወስ አቅሙ አጭርነው በሚል ፈሊጥ ይመራሉ። በዚህ ሰክረው በግለሰብም በቡድንም ዝና ሲቸራቸው የማይሳናቸው ነገር እንደሌለ ቆጥረው የኢህአዴግ ኮምትያዊ አሰራር ያረጀ የፈጀ አድርገው ቆጥረው በራሳቸው ያልተጠኑና ምን ሊያስከትሉ ይችላሉ ሳይሉ የሚወሰኑና ስልጣንን ለማራዘም ብቻ የሚያግዙ ውሳኔዎች በየቀኑ አንዳንዴም በየሰዓቱ መወሰን ጀመሩ። ለምን? ሲባሉም የአልተገናኙቶም ምክንያቶቻቸው ይደረድራሉ።

በተወካዮች ም/ቤት ሽብርተኛ ተብለው የተፈረጁ ሽብርተኛ ድርጅቶች ያለ ምንም ይቅርታ ሳይጠይቁ እንድያውም ይቅርታ እየተጠየቁ ከእስር የሚፈቱበትና ከግብፅና ከኤርትራ እንዲገቡ የተደረገበት ሁንታ ፈጠሩ። የአገሪቱ ወቅታዊ ሁኔታ አሁን በሚልዮኖች የሚፈናቀሉበትና በብዛት ግጭት እየገጠመ የታለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚሞትበት፣ የሚቆስልበት፣ ንብረቱ የሚቃጠልበትና የፌደራል መንግስት አዲስ አበባን

ብቻ የሚያስተዳድርበትና ሌላውን በመደበኛና በማሕበራዊ ሚድያ የሚመራ ሆኖ ይታያል:: በክልሎችም በኦሮሚያና አማራ ስርዓት አልበኝነት ነግሶ አስተዳዳሪዎቹ ማንም መንጋ የሚነዳቸው የህዝቡን ድምፅ ሳይሆን የፀረ ህዝቦች ማጉያ የሆኑበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን:: በሶማሊ፣ በደቡብ፣ በሀረሪና ቤንሻንጉል መረጋጋት የለም:: በአጠቃላይ የለውጡ ፍሬ ይህ ሆኖ አረፈው:: አሁንም ተጠያቂው ሌላ ነው:: ሌላ ላይ ማላከክ ተክነውበታልና:: አሁንም አደጋ ላይ ነን እየተባለ ሰሚ ጆሮ የለም:: ሚድያ እየቀረቡ ለምን መፈናቀል በዛ ሲባል በረሃብና በጉስቅልና ያለውና ያልተመለሰውን ህዝብ አብዛኛው ወደ ነበረበት ተመልሳል ይባላል:: ለተመለሰ ተፈናቃይ ምን ትሉኛላችሁ ኣቦ አታድርቁኝ! አይነት መልስ መመለስ ችግሩን አይፈተውም:: በአጠቃላይ አገሪቱ ብእረፍት ላይ ናት:: ስራ የለም! ወሬ ብቻ:: የሚድያ ላይ ሪፎርም ውጤቱ ይህ ነው::

ማጠቃለያ

የኢህአዴግ መፍረስና ህወሓትን በብአዴንና በኦህዴድ (የተጠየፉት ስም ቢሆንም!) ዒላማ ተደርጎ መመታት የተላላኪው ግንቦት ሰባት የሁለገብ ትግል ውጤት ሆኖ በአደባባይ እየተነገረ ነው:: ታድያ ግንቦት 7 በትጥቅ ትግሉ አልሆን ቢለውም፣ ሽብርም ሞካክሮ ቢከሸፈበትና አልሳካ ቢለውም፣ በፕሮፓጋንዳውም ዋሽቶም፣ አወናብዶም፣ ውዥንብር ፈጥሮም አልሳካ ቢለውም ሁለገብ የትግል ስትራተጂ ነድፎ በኢህአዴግም ውስጥ ከብዙ ልፋት በኋላ ቢሆንም ተከታዮች መልምሎም ይሁን ሌሎች መልምለው ሰጥተውት ይሁን በሚገባ በመጠቀሙ በድሉ መመዝገብ የአንበሳውን ድርሻ ተጫውተዋል እየተባለ ነው:::: ግንቦቴዎቹ አገር ቤት ከገቡ በኃላም ለውጡ ተልፈስፍሶ እንዳይቀለበስ በኢሣት ሚሳይላቸው አማካኝነት ብዙ ሚድያዎችን እየመሩ ናቸው:: ክቡር ጠ/ሚኒስተር እያሉ ሆድ እየበሉ አይደሉም እንዴ? የካቲት 11 የተገንጣይ አስገንጣይ በዓል ቀን በሚከበርበት ሀገር እንዴት ግንቦት 7ን ያክል ድርጅት የልደቱ ቀን አይከበርም? ይመጥነዋል! (ይመጥነዋል! በግንቦቴዎቹ የምትወደድ ቃል ናት ራሳቸውን ከፍ ሲያደርጉ) ስለዚህ አዋጅ ይረቀቅ:: ይፅደቅ:: ይከበር:: ለምን ይቀረናል?

የካቲት 11 በድምቀት ዛሬም ለዘላለም እየተከበረ ይኖራል!
ዘለዓለማዊ ክብር ለህዝባዊ ዓላማ ህይወታቸውን ለገበሩ!
የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት ይቀጥላል!
የፀረ ህዝቦች ግምባር በህዝቡ ትግል ይፈርሳል!

ዑስማን ሙሉአለም
ከሐራ
መጋቢት 2011

usman.mulualem@gmail.com